## ንዑስ ክፍል 2

## ኢየሱስ ክርስቶስ ለክርስቲያኖች (ለሰው ልጆች)

### 1. *ሰው ሆነ፤*

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማያት የወረደው (ዮሐ 3፥13) ጊዜው ሲደርስ ከሴት የተወለደው (ገላ 4፥3, ሉቃ 2፥1-10) በሥጋ የተገለጠው እርሱ በብርሃን ውስጥ የሚኖር መሰልና ወደር የሌለው አምላክ ሲሆን ሟች ሥጋችንን የተዋሃደው እርሱ በእኛ ሥጋ ለማጌጥ ፈልጎ ሳይሆን ለእኛ ብሎ እኛ ላይ ዲያብሎስ ያቆመውን እኛን ያስጨነቀበትን በዓለማችን ገዝፎ ይታይ የነበረውን የነቢያት ዕንባ ያልፈነቀለውን የብሉይ ኪዳን ካህናት (ሌዋውያን) የሚነፉት የመለከት ድምፅ ያላናወጠውን ቋሚ ሥራውን ያፈርስበት ዘንድ (1ዮሐ3፥8) ሞት የሆነ ዲያብሎስን ከሥልጣኑ ይሽርልን ዘንድ (ዕብ2፥14-16) የሞትና የሲኦልን መክፈቻ ከጠላታችን እጅ ይነጥቅልን ዘንድ (ራዕ1፥17-18) እኛን ኃጢአተኞችን ያድነን ዘንድ (1ጢሞ1፥15) ሕይወታችንን አጥተን ወደ መቃብር ለምንወርደው ሕይወትን ሊያበዛልን (ዮሐ10፥10) ወደ ሕይወት የሚወስደው መስመር በሱራፌል ሠይፍ ስለተዘጋብን መንገድ ሊሆነን (ዮሐ14፥6) ሌሎችንም ጎደሎዎቻችንን ሊሞላ ሰው ሆነ እንጂ በመለኮት ዘንድ ሰው መሆን የሚያስቀና ሣይሆን የሚያሳዝን ነበር። ነገር ግን "ዘበእንቲአነ ለሰብእ ወበእንተ መድኃኒትነ ወረደ እምሰማያት ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም ቅድስት ድንግል" ስለእኛ ስለ ሰዎች እኛን ለማዳን ከሰማያት ወረደ በግብረ መንፈስ ቅዱስም ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆነ በማለት 318ቱ ሊቃውንት እንደተናገሩ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ነው ሰው የሆነ።



www.ethiopianorthodox.org

### 2. *ስለ እኛ ተጠመቀ፤*

ኢየሱስ ክርስቶስ ዮሐንስ ከሚያጠምቃቸው ኃጢአተኞች እንደ አንዱ ሆኖ ነው የተጠመቀው ስለእኛ ጽድቅን ሁሉ ሊፈጽም ቅዱስ ቅዱሳን የሆነው ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ከኃጢአተኞች የሰው ዘሮች መካከል አይቶ አባቱ የምወደው የምወልደው ለተዋሕዶ ለመሥዋዕትነት የመረጥኩት የምመለክበት የምሰገድበት ልጄ ነው ብሎ ሲናገር እኛ ኃጢአተኞችም በልጁ በኩል ታይተን የምወዳችሁ ልጆቼ ያሠኘን ዘንድ እርሱ ጻድቀ ባሕርይ ሲሆን ከእፉኝት ልጆች መካከል በመታየቱ እንከብር ዘንድ ስለ እኛ ተጠመቀ በተጠመቀበትም ወቅት የዕዳ ደብዳቤያችን ተቀደደ (ቆላ 2፥14)

### 3. *ስለእኛ በደል ደቀቀ፣ ቆሰለ፣ ታመመ፤*

በነቢዩ "ተጨነቀ ተሠቃየም አፉንም አልከፈተም ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፣ በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ። ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፤ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር። በአፉም ተንኮል አልተገኘበትም ነበር፤ እግዚአብሔር በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፤ ነፍሱን ስለኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል ዕድሜውም ይረዝማል። የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል" ተብሎ (ኢሳ 53፥7-10) በዘካርያስም "ሰውም ይህ በእጅህ መካከል ያለ ቁስል ምንድር ነው? ይለዋል እርሱም በወዳጆቼ ቤት የቆሰልሁት ቁስል ነው ይላል" ተብሎ እንደተጻፈ (ዘካ 13፥6) በሐዋርያውም "ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤

በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ እንደበጎች ትቅበዘበዙ ነበርና አሁን ግን ወደነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል" (1ጴጥ 2÷24-25) ተብሎ እንደተጻፈ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመተላለፋችን ተንገላታና እኛ በእርሱ ቁስል ተፈወስን ስሙ ቡሩክ ይሁን።

## 4. ስለ እኛ ተሰቀለ፤

ሐዋርያው "በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለእኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል የአብርሃም በረከት ወደአሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ" (ገላ 3÷13-14) አለ 318ቱ ሊቃውንትም "ኮነ ብእሴ ወተሰቅለ በእንቲአነ በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ - ፍጹም ሰው ሆነ በጰንጦስ ሰው በጲላጦስ ዘመን ስለእኛ ተሰቀለ" ብለዋል። በመጽሐፈ ኪዳንም "ተሰቅለ በእንቲአነ ወበመስቀሉ ኮነ ሕይወትነ ጽንዕነ ቤዛነ" ስለእኛ ተሰቀለ በመስቀሉም ኃይላችን ጽንዓተ ነፍሳችን፣ ቤዛችን ሆነልን ተብሎ ተጽፎአል።

ክርስቲያን ሆይ እጆቹ እግሮቹ የተቸነከሩ ስለአንተ እንደሆነ አትዘንጋ "የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው?" (ገላ 3÷1) ተብሎ እንደተጻፈ በዕብራውያን መልእክትም "እንግዲህ እንደነዚህ ያሉ ምስክሮች እንደደመና በዙሪያችን ካሉልን እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሶ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ (ዕብ 12÷1-3) እንደተባለ በብሉይ ኪዳንም "እግዚአብሔርም ሙሴን እባብን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል



www.ethiopianorthodox.org

የተነደፈውም ሁሉ ሲያየው በሕይወት ይኖራል አለው። ሙሴም የናሱን እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ፤ እባብም የነደፈችው ሰው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ።" (ዘኁ 21÷8-9) ተብሎ እንደተጻፈ ዓይንህን ከተሰቀለው ጌታህ አታርቅ እርሱንም ዓይኖችህ ዘወትር ይመልከቱ። (ዮሐ 3፤14-16) ራሱን በመስቀል ላይ የሠዋልህ ከሞትና ከኩነኔ የታደገህ ራሱን አሳልፎ የሰጠልህ መድኃኒትህ እሱ ነውና እየው ተመልከተው አስተውለው፣ የዐይንህ አምሮት የልብህ ፍላጐት እርሱ ይሁን እሱን ስሙ ሁሉ ሊያይ የሚገባው የእግዚአብሔር ማዳን ላንተ ያዘጋጀው ትድግናው እሱ ነውና (ሉቃ.2÷24-38፣ ሉቃ.3÷3-6)።

## 5. ስለእኛ ስለሰዎች ሞተ፤

ሞት የኃጢአት ደመወዝ መሆኑን "የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው። የእግዚአብሔር የጸጋ ሥጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘለዓለም ሕይወት ነው።" (ሮሜ 6÷23) ተብሎ በተጻፈው መለኮታዊ ቃል መረዳት ይቻላል። ሞት የኃጢአት ደመወዝ ከሆነ ኃጢአት ለሌለበት ለወልደ አብ ለወልደ ማርያም ሞት ባልተገባውም ነበር ነገር ግን "እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብሎ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለኃጢአታችን ሞተ ተቀበረም፣ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ።" (1ቆሮ 15÷3-4) "ይህን ስለቈረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና አንዱ ስለሁሉ ሞተ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ በሕይወትም ያሉት ስለእነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደፊት ለራሣቸው እንዳይኖሩ ስለሁሉ ሞተ።" (2ቆሮ 5÷14-15) ተብሎ እንደተጻፈ እርሱ የሞተው ስለእኛ ስለኃጢአታችን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሞተለት የሚያምን ;ኃጢአተኛ የክርስቶስ ሞት ስለእርሱ ተቆጥሮለት ለመንግሥተ ሰማያት ይበቃ ዘንድ ከሞት ወደ ሕይወት ይሻገር ዘንድ ክርስቶስ ስለ ሰው ሞተ። ቅዱስ ኤፍሬምም "ዘዚአነ ሞተ ነሥአ ወእንቲአሁ ሕይወተ ወኀበነ ዘሎቱ ክብር ወስብሐት" ማለት ክብር

የክብር ክብር ያለው እርሱ የኛን ሞት ተቀብሎ የሱን ሕይወት ሰጠን ብሎ የተደረገልንን መዳን ሰበክልን (የዓርብ ውዳሴ ማርያም)።

ክርስቲያን ሆይ አንዱ ስለሁላችን ሞቶአልና በሞቱም ጸድቀናልና በደሙም ከኃጢአታችን ታጥበናልና ሁላችንም ከሐዋርያው ከቅ/ዮሐንስ ጋር እንዲህ እያልን እንዘምር

"ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ ለእርሱ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን አሜን።" (ራዕ 1፥6-7)

## 6. ስለእኛ ተቀበረ፤

ኢየሱስ በመቀበሩ እኛ ከመቃብር በላይ በትንሣኤ ሙታን እንድንሆን አድርጎናል፤ መቃብር ኃይሉን ያጣው ሙታንን ይዞ የሚያስቀርበት ሥልጣኑን የሻረው ፈርሶ በስብሶ መቅረትን ያጠፋው በመቃብር ውስጥ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በማደሩ ነው።

ክርስቲያኖች ሆይ ከሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ ጋር "ዳሩ ግን ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሲለብስ በዚያን ጊዜ ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ" ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል። "ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሣትህ የት አለ? የሞት መውጊያው ኃጢአት ነው የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን" እያልን እንዘምር (1ቆሮ 15፥54-57)

## 7. ስለእኛ ተነሣ፤

ቤተክርስቲያን ስለኢየሱስ ትንሣኤ ስታስብ ስትመሰክርም የምታስታውሰው ሁለት ነገሮችን ነው።



www.ethiopianorthodox.org

አንደኛ ኢየሱስ ክርስቶስን "እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና።" እንዳለ ቅ.ጴጥሮስ (ሐዋ 2፥24) "እነርሱም በዚህ ሲያመነቱ እነሆ ሁለት ሰዎች የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው ወደ እነርሱ ቀረቡ ፈርተውም ፊታቸውን ወደምድር አቀርቅረው ሳሉ እንዲህ አሉአቸው ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም።" አሉአቸው እንደ ቅዱስ ሉቃስ (ሉቃ 24፥4-5) "ባየሁትም ጊዜ እንደሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እነሆም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ሕያው ነኝ የሞትና የሲኦል መክፈቻ አለኝ" (ራዕ 1፥17-18) ተብሎ እንደተጻፈ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ መነሣቱን እናስባለን፣ እናስተምራለን። በሞቱ አድኖ በትንሣኤው ስላጸደቀን።

ሁለተኛ ደግሞ "አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና፤ ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል ክርስቶስ እንደበኩራት ነው።" (1ቆሮ 15፥20-23) እንዲሁም "እርሱም የአካሉ ማለት የቤተክርስቲያን ራስ ነው እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ መጀመሪያ ከሙታንም በኩር ነው" (ቆላ 1፥18) ተብሎ እንደተጻፈ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የእኛ ትንሣኤ በኩር መሆኑን እኛም እንደእርሱ የምንነሣ መሆኑን ነው። ስለዚህም ሐዋርያው "ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሣ የሚሰበክ ከሆነ ግን ከእናንተ አንዳንዶቹ ትንሣኤ ሙታን የለም እንዴት ይላሉ? ትንሣኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣማ ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት ደግሞም ክርስቶስን አስነሥቶታል ብለን በእግዚአብሔር ላይ ስለመሰከርን ሐሰተኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል። ሙታን ግን የማይነሡ ከሆነ እርሱን አላስነሣውም

ሙታን የማይነሡ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሣማ ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት እስከአሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ። እንግዲያስ በክርስቶስ ያንቀላፉት ደግሞ ጠፍተዋላ፣ በዚህች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን።" (1ቆሮ15፥12-19) በማለት ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ የቆሮንቶስን መናፍቃን ወቅሶአል፤ ምዕመናን ወገኖች በትንሣኤው ስለተነሣን የኢየሱስ ትንሣኤ ስለእኛ መዳን ዐቢይ ምሥጢር አለው። በአዳም በደል ወደመቃብር የወረድነው በክርስቶስ ተነሥተናል፤ በመጀመሪያው ሰው በደል የተከፈው የመቃብር አፍ በክርስቶስ ትንሣኤ ድል ተነሥቷል።

## 8. ስለእኛ ወደሰማይ ዐረገ፤

የቤተክርስቲያናችን መጽሐፍ "ዐርገ እግዚአብሔር ከመያለቡ ዕርገተ ጻድቃን፤ እግዚአብሔር ወልድ የጻድቃንን ዕርገት ያስገኘዝብ ዘንድ ዐረገ" ይላል በመጽሐፍ ቅዱስ ስለኢየሱስ ዕርገት የተጻፈውን እንመልከት "ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ።" (ማር16፥19) "እስከ ቢታንያም አወጣቸው እጆቹንም አንሥቶ ባረካቸው ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ ወደሰማይ ዐረገ" (ሉቃ 24፥50-51) "ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ደመናም ከዐይናቸው ሰውራ ተቀበለችው እርሱም ሲሄድ ወደሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ ደግሞም የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው" መጽሐፈ ሕይወት መጽሐፍ ቅዱስ (የሐዋ1፥9-11) ሠለስቱ ምዕትም "ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ- በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ" ብለዋል። ታዲያ ኢየሱስ ዐረገ ማለት በታሪክ ደረጃ የሚታወስ ነው እንጂ ለእኛ ምን ያደርግልናል



www.ethiopianorthodox.org

ስለእኛ ዐረገ ተባለ የሚል ቢኖር በእርሱ ዕርገት ምድራውያን የነበርነው በሞት ከምድር ጋር የተቀላቀልነው ከፍ ከፍ አልን ሕይወታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ተሰወረ "እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም፤ ሞታችኋልና ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ።" (ቆላ 3፥1-4) ተብሎ የተጻፈውን ቃለ መጽሐፍ ልብ እንበል። አሁን በሞቱ ሞትን (ለኃጢአት) በትንሣኤውም ተነሣን በዕርገቱም ዐረግን ሰማያውያን ሆንን ሕይወታችንም ከኢየሱስ ጋር ወደሰማይ ተሰወረ (ዐረገ) በመምጣቱም ይገለጣል። ከላይ የጠቀስነው የቤተክርስቲያናችን መጽሐፍ እንዳለው የኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት የጻድቃንን ዕርገት ያመለክታል።

ቅድስት ቤተክርስቲያንም "ላዕለ ይኩን ኀሊናክሙ በሰማይ የሀሉ ልብክሙ አእምሩ ኀበ ዘትቀውሙ ወስምኡ ቃለ ጽድቅ ወአጽምኡ ዜና ሠናየ" በማለት ስትቀድስ ትሰማለች።

ትርጉሙም "ኀሊናችሁ በላይ ክርስቶስ ባለበት ይሁን ልባችሁም በሰማይ ይኑር የቆማችሁበትን እወቁ፤ የጽድቅ ቃልን ስሙ መልካም ዜና ወንጌልን አድምጡ" ማለት ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም "... እስመ ኃበ ሀሎ ርዕስ ህየ ይሄሉ አካል..." (...ራስ /ክርስቶስ/ ባለበት አካል /ቤተክርስቲያን/ ትኖራለች...) ብሎአል።

## 9. ስለእኛ በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ፤

"ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ" (ማር 16፥19) "እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ

ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ" (ዕብ 1፥3) "ከተናገርነውም ዋና ነገሩ ይህ ነው በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀካህናት አለን።" (ዕብ 8፥1) ተብሎ እንደተጻፈ ኢየሱስ ማረጉ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ከመለኮታዊ ክብሩ ተራቁቶ ኑሮ ወደመለኮታዊ ክብሩ በተመለሰ ጊዜ የተራቆተ መለኮታዊ መንበሩን ተቆጣጠረ ለማለት ሳይሆን ይህ ቃል የሚያመለክተው እኛን ለማዳን ወረደ የተባለው ለምልዐተ መለኮቱ ውሣኔ የሌለው እርሱ ሥራውን መጨረሱን በእርሱ ክብር መቀመጣችንን ነው የሚገልጸው። ተቀመጠ የተባለውም ክብር የለሽ የነበረውን የሰው ልጆችን ባሕርይ ነው የሚያመለክተው እንጂ ወልድ ለመለኮታዊ ዙፋኑማ አዲስ አይደለም፤ በአብ ቀኝ ኢየሱስ እንደተቀመጠ እኛም እንደከበርን በመቀመጡም የከበርነውን ክብር በሚመለከት "በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ከእርሱ ጋር አስነሣን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን" (ኤፌ 2፥6-7) ተብሎ የተጻፈውን ማንበብ በቂ መረጃ ነው።

በየማነ አብ የተቀመጠው ወልደ አብ ክርስቶስም ዕድል ፈንታችን ከእርሱ ጋር እንደሚሆን ተስፋ ሰጥቶናል፤ እንዲህ ብሎ "የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል" (ዮሐ 12፥26) "...እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ" (ዮሐ 14፥3) "...ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ" ብሎ (ራዕ 3፥21) የሊቀካህናትነት ጸሎቱንም ሲጸልይ "...አባ እለሰ ወሀብከኒ እፈቅድ ከመየሀልዉ ኀበ ሀሎኩ አነ ምስሌየ ከመ ይርአዩ ስብሐትየ ዘወሀብከኒ" ብሏል። ይህም ማለት "አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድኸኝ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ" (ዮሐ 17፥24) ማለት ነው። ቅ/ጳውሎስም ይህንን ተስፋ



www.ethiopianorthodox.org

እምነት እንደምንወርስ ሲናገር "ወታበውእ ውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ኀበ ቦአ ኢየሱስ ሐዋርያነ እምቅድሜነ ሊቀ ካህናት ... ከዊኖ ዘለዓለም" ብሏል (ዕብ6፥20) ይህንን ቃል ብሔራውያን፣ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እንድምታ ትርጉማቸው ሲተረጉሙት "እንደመልከ ጼዴቅ ባለ ሹመት ዘለዓለም አገልጋያችን፣ አስታራቂያችን፣ ፊታውራሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደገባበት ውሳጤ መንጦላዕት የምታገባ ሃይማኖት ናት" ብለዋል እንድምታ ትርጓሜ ዕብራውያን ይመልከቱ)።

እኛም ዛሬ በዚህ ተስፋ ጸንተን ከዮሐንስ ጋር "በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘለዓለም እስከዘለዓለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለበጉ ይሁን" (ራዕይ 5፥13-14) እያልን እንዘምር።

## <u>ጥያቄዎች</u>

1. ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ሰው ሆነ?
2. ለምን ተጠመቀ?
3. ለምን ደቀቀ ቆሰለ ተሰቃየ ታመመ?
4. ለምን ተሰቀለ?
5. ለምን ተቀበረ?
6. በትንሣኤው ምን አገኘን?
7. በዕርገቱ ቤተክርስቲያን ምን አገኘች?
8. በአባቱ ቀኝ መቀመጡ እሱነቱ በምን ይታወቃል?

መምህር ልዑለ ቃል አካሉ ዓለሙ
መ.ሣ.ቁ. 270
አዲስ አበባ
Leulekal Akalu Alemu
266 Robbin Street
Decatur G.A. 30030
U.S.A.